መልእክት አራት

## ታማኝ እና ልባም ባሪያ በመሆን
## ለጌታ መምጣት ራሳችንን ማዘጋጀት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:- ማቴ. 24፡45-51

I. **“እንኪያስ ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተ ሰዎች ላይ የሾመው ታማኝና ልባም ባሪያ ማን ነው? ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ባለው ሁሉ ላይ ይሾመዋል”—ማቴ. 24፡45-47፡-**

  ሀ. በእምነት የሆነው የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ የእርሱ “የቤተሰብ” ኢኮኖሚ፣ የቤተሰቡ አስተዳደር ነው፣ ያም ራሱን ለመግለጥ ቤት፣ ቤቱም ቤተ ክርስቲያን፣ የክርስቶስን አካል ይኖረው ዘንድ ራሱን ወደ መረጣቸው ሕዝቡ ውስጥ ማደል ነው—1 ጢሞ. 1፡4፤ 3፡15፤ ኤፌ. 2፡19።

  ለ. ታማኙ እና ልባሙ ባሪያ ለአማኞቹ ክርስቶስን እንደ “ምግብ” የሚያድል በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ያለ መጋቢ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ ነው—1 ቆሮ. 9፡17፤ ኤፌ. 3፡2፤ 1 ቆሮ. 4፡1፤ 1 ጴጥ. 4፡10፡-

    1. ታማኝነት የሚታየው ወደ ጌታ ሲሆን (1 ቆሮ. 4፡2፤ 7፡25)፣ ልባምነት ተግባር ላይ የሚውለው ከአማኞች አንጻር ነው (ተዛ. ቆላ. 1፡28፤ 2 ዜና. 1፡10፤ ፊልጵ. 4፡5)።

    2. በመንግሥተ ሰማያት መገለጥ ውስጥ፣ ጌታ ታማኙን ባሪያ ባለው ሁሉ ላይ ይሾመዋል፤ ይህ ለባሪያው ሽልማት ይሆናል—ማቴ. 25፡21፣ 23።

  ሐ. *ምግባቸውን ይሰጣቸው* የሚለው በቤተ ክርስቲያን ላሉ አማኞች አቅርቦት ለመስጠት የእግዚአብሔርን ቃል እና ክርስቶስን እንደ የሕይወት አቅርቦት ማገልገልን ያመለክታል—24፡45፤ ዮሐ. 6፡57፣ 63፣ 68፡-

    1. ሌሎችን መመገብ እንችል ዘንድ እንደ መንፈሳዊ ምግባችን ጌታን እንድንደሰት፣ ቃሉን በሁሉም ዓይነት ጸሎቶች መቀበል እና ከብዙ አስተውሎት ጋር ቃሉን ጮክ ብለን በመናገር፣ ቃሉን ማሰላሰል ያስፈልገናል—ኤፌ. 6፡17-18፤ መዝ. 119፡15 (የግርጌ ማስታወሻውን ተመልከቱ) ፣ 48፣ 148፣ ኢያ. 1፡8፤ ዘሌ. 11፡2-3፤ ሕዝ. 3፡1-4፤ ቆላ. 3፡16።

    2. በጸሎት እና በቃሉ አገልግሎት በትጋት መቀጠል ያስፈልገናል—ሐዋ. 6፡4፤ ተዛ. ዕብ. 7፡25፤ 8፡2።

    3. ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት ትንቢትን መናገር ያስፈልገናል—በመንፈሳችን መንቀሳቀስ በኩል በመንፈስ ቅዱስ የጊዜው እና ትኩስ ማነሳሳት፣ መቀባት እና ማብራት ሥር ከዚህ ሕይወት ሕያው ቃላት ያየነውን መናገር ያስፈልገናል—1 ቆሮ. 14፡4፤ ሐዋ. 5፡20፤ 4፡20፤ 22፡15።

    4. ራሳችንን እና በእንክብካቤያችን ሥር ያሉትን ለመመገብ ሕይወትን የሚሰጠውን መንፈስ እንደ አቅርቦታችን፣ እንደ መንፈሳዊ ምግብ ለመቀበል ራሳችንን ወደ እግዚአብሔር ውስጥ መጸለይ ያስፈልገናል—ሉቃ. 11፡1-13።

    5. ሕይወትን የሚሰጡ “ጠያቂዎች”፣ ለሌሎች ሕይወት መስጠት የሚችለው ሕይወት የሚሰጠው መንፈስ መተላለፊያዎች መሆን ያስፈልገናል—1 ዮሐ. 5፡16።

    6. ለሚያበራው ምስክር፣ ለኢየሱስ ምስክር ወደ መቅረዙ ውስጥ መንፈስን ለማፍሰስ፣ እንደ የደስታ ዘይት ባለማቋረጥ በትኩሱ፣ በአሁኑ እና በተጠናቀቀው መንፈስ በመሞላት “ትኩስ የዘይት ልጆች” መሆን ያስፈልገናል—ዘካ. 4፡6፣11-14፤ ፊልጵ. 1፡25፤ ራእ. 3፡18፤ ማቴ. 25፡9፡-

      ሀ. ለወርቃማዋ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም መገንባት ንጹሕ የወርቅ መቅረዝ መሆን እንድንችል እንደ ወርቃማው ዘይት በመለኮታዊው ባህሪው እግዚአብሔርን ይበልጥ እንድናገኝ በየዕለቱ ዋጋውን መክፈል ያስፈልገናል—2 ጴጥ. 1፤4፤ ራእ. 3፡18፤ 1፡20፤ 21፡18፤ ማቴ. 25፡8-9።

      ለ. ይህን ጉዳይ ዛሬ በልምምዳችን እየተገበርን ሳለ፣ ከውስጣችን የሚፈሰው መንፈስ እግዚአብሔር እንደሆነ እናያለን፣ እግዚአብሔር ደግሞ ወርቅ ነው፤ ስለዚህ ዘይትን በማቅረብ ክርስቶስን ለሌሎች ስናገለግል፣ በእርግጥ እያቀረብን ያለነው እግዚአብሔርን ነው፤ እግዚአብሔር ከእኛ ውስጥ ወደ እነርሱ ውስጥ ይፈሳል—ዘካ. 4፡12-14፤ ዮሐ.. 7፡37-39፤ 2 ቆሮ. 3፡3፣ 6. 8፤ ሉቃ. 10፡34።

II. **“ያ ክፉ ባሪያ ግን። ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ፥ ባልንጀሮቹን ባሮች ሊመታ ቢጀምር ከሰካሮችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ፥ የዚያ ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል፥ ከሁለትም ይሰነጥቀዋል፥ እድሉንም ከግብዞች ጋር ያደርግበታል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል”—ማቴ. 24፡48-51፡-**

ሀ. ጌታችን ይዘገያል ብለን በልባችን ማሰብ የአሁኑን ክፉ ዘመን መውደድ እና የጌታን መገለጥ አለመውደድ ነው—2 ጢሞ. 4፡8፤ 10፡-

1. መምጣት የሚለው የግሪኩ ቃል “ፓሮዚያ” ነው ያም “መገኘት” ማለት ነው፤ የጌታን መገለጥ፣ የእርሱን መምጣት ለመውደድ፣ ዛሬ የእርሱን መገለጥ፣ የእርሱን መገኘት መውደድ አለብን—ማቴ. 24፡3፣ 37፣ ሐዋ. 26፡16፤ 2 ቆሮ. 2፡10፤ ከእንግሊዘኛው የመዝሙር መጽሐፍ #389።
2. ዛሬ እስካለን ድረስ፣ የእርሱን መምጣት እየተጠባበቅን እና የእርሱን መምጣት እንደ ማስጠንቀቂያ፣ ማበረታቻ እና ማነሳሻ በመውሰድ ጌታን እና መገለጡን መውደድ አለብን—2 ጢሞ. 4፡8፤ ፊልጵ. 3፡20፤ ራእ. 22፡12።
3. ለመምጣቱ ነቅተን የምንጠባበቅ እና የተዘጋጀን መሆን ያስፈልገናል—ማቴ. 25፡13፤ 24፡44፤ ራእ. 19፡7።
4. በእግዚአብሔር ፊት ባለጠጎች መሆን እንጂ ለራሳችን መዝገብን ባለማከማቸት፣ ከስግብግብነት መጠንቀቅ አለብን—ሉቃ. 12፡16-20፤ 2 ቆሮ. 6፡10፤ ኤፌ. 3፡8።
5. እግዚአብሔር የሚፈርድበትን እና ፈጽሞ የሚያጠፋውን ክፉውን ዓለም ባለመውደድ እና እንደ ውድ መዝገብ ባለመያዝ የሎጥን ሚስት ማስታወስ ያስፈልገናል—ሉቃ. 17፡28-32።
6. ጌታ የሚመጣበት ቀን በድንገት እንደ ወጥመድ እንዳይመጣብን ነቅተን መጠበቅ እና መለመን ያስፈልገናል—21፡34-36፣ ተዛ.ጥ. ማቴ. 2፡3።
7. “ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና!”—ይህ ጌታን እና የእርሱን መገለጥ የሚወዱቱ ናፍቆት፣ ጩኸት እና የማያቋርጥ ጸሎት መሆን ይገባዋል—ራእ. 22፡20፤ ቲቶ 2፡12-13።

ለ. ባልንጀሮች ባሮችን መምታት ባልንጀሮች አማኞችን መበደል ነው—ተዛ.. ሐዋ. 9፡4፡-

1. ባልንጀሮች አማኞችን መፍረድ ወይም መኮነን ሳይሆን ለእነርሱ ደግ መሆን፣ መራራት እና እንዲያውም እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳለን ይቅር ማለት ይገባናል—ሉቃ. 6፡37፤ ኤፌ. 4፡31-32።
2. ወንድሞቻችንን መሳደብ ወይም መንቀፍ ሳይሆን ከራሳችን ይልቅ እጅግ በጣም ጥሩ እንደሆኑ ማሰብ ያስፈልገናል—1 ቆሮ. 6፡10-11፤ ፊልጵ. 2፡3፣ 29።
3. በባልንጀሮች አማኞች ላይ መሰልጠን (ለእነርሱ ውሳኔዎችን እንደመወሰን ያለ ነገር) ሳይሆን ሕይወትን እንደሚሰጠው መንፈስ ከሞት በተነሣው ክርስቶስ እነርሱን በመመገብ እነርሱን እንደ ባሪያ ማገልገል አለብን—1 ጴጥ. 5፡3፤ ማቴ. 20፡25-28፤ ተዛ. ዘኁ. 17፡8።

ሐ. ከሰካሮች ጋር መብላት እና መጠጣት በዓለማዊ ነገሮች ከሰከሩ ዓለማውያን ሰዎች ጋር መወዳጀት ነው፡-

1. ከመለኮታዊ ባህሪያቸው እና ከቅዱስ መቆሚያቸው የተነሣ አማኞች ከማያምኑት ጋር አብረው መጠመድ የለባቸውም፤ ይህ ለጋብቻ እና ለቢዝነስ ብቻ ሳይሆን፣ በአማኞች እና በማያምኑት መካከል ላሉ ለሁሉም አይነት የቅርብ ግንኙነቶች መተግበር አለበት—2 ቆሮ. 6፡14፤ 1 ቆሮ. 15፡33፤ ተዛ. ምሳ. 13፡20።
2. ክፉ የወጣትነትን ምኞቶችን መሸሽ እና በንጹሕ ልብ ጌታን ከሚጠሩት ጋር ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስ መከታተል ያስፈልገናል—2 ጢሞ. 2፡22።

መ. ታማኝ እና ልባም የሆነው ባሪያ በመንግሥቱ መገለጥ በሥልጣን መግዛትን ሲሸለም ክፉው ባሪያ ግን ከክርስቶስ፣ ከመንግሥቱ ክብር እና በመንግሥቱ ውስጥ ካለው ክቡር መገኘቱ ይቆረጣል—ማቴ. 24፡47፣ 51፡-

1. ከመንግሥቱ መገለጥ መቆረጥ ለቅሶ እና የጥርስ ማፋጨት በሚሆንበት በውጪ ወዳለው ጨለማ ውስጥ መጣል ነው፡-
   ሀ. በውጪ ያለው ጨለማ በመንግሥቱ መገለጥ ካለው ብሩህ ክብር ውጪ ያለው ጨለማ ነው—16፡28፤ 25፡30።
   ለ. ለቅሶ መፀፀትን ሲያመለክት፣ የጥርስ ማፋጨት ደግሞ ራስን መውቀስን ያመለክታል።
2. በሺው ዓመት መንግሥት ውስጥ ከክርስቶስ ጋር በአሕዛብ ላይ መንገሥ ታማኝ እና ልባም ለሆኑት ባሮቹ ሽልማት ይሆናል—ራዕ. 2፡26፤ ሉቃስ 19፡17-19

© 2023 Living Stream Ministry